# ኢሕአፓ ለምን ተከፈለ? ዛሬስ ምን መደረግ አለበት?

ፀሐፊ ፦ ነሲቡ ስብሐት
ከ ፦ ሰሜን አሜሪካ
ቀን ፦ ታህሳስ 29 ቀን 2012 ዓ.ም.

በቅድሚያ ለክርስትና እምነት ተከታዮች “እንኳን ለብርሃነ ልደቱ አደረሳችሁ” እላለሁ።

በዚህ ርዕስ አጭር ጽሁፍ መፃፍ ከባድ ነው። ኢሕአፓን ያህል አንጋፋ ድርጅት ለመከፈል ብዙ ውጣ ውረድ፣ ውይይት፣ ንትርክ፣ ተደርጎበት በወቅቱ የነበሩትን አባላት አሳዝኖ የተከሰተ ሂደት ነው። በኢሕአፓ ታሪክ ተወደደም ተጠላ ይህ የመከፈል ጉዳይ በመጽሐፍ መልክ እንኳ ቢቀርብ እንዴት ነፃ ሆኖ ይቀርባል? የሚለው ይፈታተናል። ያም ሆነ ይህ መፃፉ አይቀርም። ለምን ተከፈለ? እንዴት ተከፈለ? ዋናው ምክንያት ምንድነው? ሂደቱስ? ኢሕአፓን ያህል ተመክሮ ያለው ፓርቲ እንዴት የቅራኔ አያያዝ ጥበቡ፣ ዕውቀቱ አነሰውና ለዚህ አሳፋሪ ድርጊት እጁን ሰጠ? ሂደቱ ከተከሰተም በኋላ መከፈሉን የሰሙ ደጋፊዎቹ፣ የቀድሞ አባላቱ እንደገና አንድ ለማድረግ ያደረጉት ጥረት ምነው ሳይሳካ ቀረ? ወዘተ. መልሱ እንኳንስ ሀገር ቤት ላሉት የኢሕአፓ የቀድሞ አባላት፣ ደጋፊዎችና ቤተሰቦች ሌሎችም ይቅርና ሲከፋፈል ለነበሩት አባላት እንኳ ያስደመመ ጉዳይ ነው።

ለዚህ ጽሁፌ መነሻ የሆነኝ በቅርቡ ሀገር ቤት የሚንቀሳቀሰው የ“ኢሕአፓ” ሊቀመንበር ወ/ሮ ቆንጂት ብርሃን ታህሳስ 23 ቀን 2012 ዓ.ም. (January 2, 2020) በኢሳት አዲስ አበባ “መክሊት” (https://www.youtube.com/watch?time_continue=2&v=qlgxh-a3b-0&feature=emb_logo) ዝግጅት ላይ የሰጡት ክፍል 2 ምላሽ ነው። “ኢሕአፓ የተከፈከው ሀገር ቤት እንግባ ወይስ አንግባ በሚል አለመግባባት ነው።” ወ/ሮ ቆንጂት በሙሉ ልብነት? በመጠራጠር? ባለማወቅ? በመሰለኝ? የመለሱት ምላሽ።

በዚህ ጉዳይ ብዕሬን ላነሳ የተገደድኩት ጉዳዩ የሚመለከተን የኢሕአፓ የቀድሞ አባላት በርካቶች ነንና ነው። የኢሕአፓ መከፈል ጉዳይ ከጅምሩ፣ ውዝግቡ አስታከ፣ ለመከፈል እስከበቃበት፣ ከተከፈለም በኋላ በሁለቱ ወገኖች ያለው ውዝግብና ዳግም የተካሄደው የአባላት ብተና መጤን ይገባዋል። በሁለቱም ኢሕአፓዎች በኩል መረጃን ተገን አድርጎ ለማቅረብ በዚህ አጭር ጽሁፍ የሚሆን አይደለምና ወደፊት ጊዜ ያወጣው ይሆናል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ሐምሌ 20 ቀን 2010 ዓ.ም. (July 27, 2018) በዋሽንግተን ጉብኝታቸው በመላው ዓለም ላሉ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች፣ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሲቪክ ማህበራት ባደረጉት ጥሪ መሠረት ያለምንም ማጋነን ጥሪውን ተቀብሎ ያልገባ ቢኖር በአቶ እያሱ ዓለማየሁ የሚመራው ኢሕአፓ ነው።

ኢሕአፓ ጥቅምት 18 ቀን 2000 ዓ.ም. (october 29, 2007) ሲከፈል እራሱን “ኢሕአፓ ዴሞክራሲያ” ያለው ቀጥሎም በሰኔ 27 ቀን 2007 ዓ.ም. ጋዜጣዊ መግለጫው መሠረት ኢሕአፓ አንድ ሆነ በማለት ወደ “ኢሕአፓ አንድነት” የተቀየረው በጥሪው ወቅት ሌላ ኢሕአፓ እንደሌለ በማስመሰል በአቶ መርሻ ዮሴፍ ሊቀ መንበርንርት ኢሕአፓ ብለው ገብተዋል። በቅርቡም ታህሳስ 8 እስከ 9 ቀን 2012 ዓ.ም. በአካሄዱት ጉባኤ መሠረት ከምርጫ ቦርድ ሕጋዊነትን ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ለመውሰድ በመጠባበቅ ላይ ናቸው።

ኢሕአፓ ሲጠራ እንኳን ሰዉ አርማውን ያውለበለቡ የኤሌክትሪክ ሽቦዎች፣ መፈክሩን የተሸከሙ አጥሮች ይነቃነቃሉ። የመንደር ውሾች ሳይቀሩ ቢያላዝኑ "ኢሕአፓ" የሚለውን ጽሁፍ ይዘው ዞረዋልና አያስደንቅም። በከተማው፣ በገጠሩ ተሰልፈው የነበሩ የትላንት ወጣት የዛሬ አባወራዎች፣ የቤት እመቤቶች በመላዋ ኢትዮጵያ ቀላል አይደሉም። በመቶ ሺህ የሚቆጠር ቤተሰብ ቢያንስ አንድ የቤተሰብ አባል በትግሉ ተሰውቶበታል። የትላንት ሕጻናት በትንሹ የዛሬ 45 ዓመት የዕድሜ ባለጸጋ ለኢሕአፓ የተሰለፉ ወንድም፣ እህት፣ እናት፣ አባት፣ ዘመድ፣ ጓደኛ ያጡት በርካታ ናቸው። እነዚህ በሕይወት ያሉ ኢትዮጵያውያን ዘር፣ ሃይማኖት፣ እድሜ ሳይለይ ያሰባሰባቸው ኢሕአፓ ለ40 ዓመት እንኳን ለሀገር ሊበቃ  ስሙ ሲጠራ የሚያባንናቸው ደርግና ወያኔዎች ሀገር አሳጥተውት "ስደተኛው ኢሕአፓ" አስብለውታል። ይህን ሁሉ አሳዛኝ ጭካኔ ተቋቁሞ ዛሬ ማንም ይምራው ማን ኢሕአፓ ይጠራችኋል ሲባል "ስምህ ብቻ ሕይወቴ" ብለው የሚመጡ ዜጎች አሁንም በ100 ሺህዎች እንደሚቆጠሩ፣ እንደሚሆኑ ጥርጣሬ ሊገባን አይገባም። ለዚህም ጥሪ ጥንት ያሰባሰባቸው ከእስላሙ ህብረተሰብ፣ ክርስቲያኑ፣ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግሬ፣ ጉራጌ፣ ወላይታ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ አደሬ፣ ጉጂ ቢዘረዘር የማያልቅ የህብረተሰብ ክፍል ከኤርትራ ጨምሮ በመምጣት ኢትዮጵያን ወደ ድሮው አንድነቷ ሊመልሳት የሚችል እምቅ  ኃይል እንደሚኖረው መገመት ይቻላል። ይህ ግና ዘረኝነት የበላይነቱን ለተጎናጸፈባት ሀገር መታለፍ ያለበት መሰናከል ቀላል አይደለም። ይህንን ነጥብ ያነሳሁት ሁሉም የየራሱን ታሪክ ለማውራት፣ ለማድመጥ፣ ለመቆዘም፤ ለማልቀስ፣ ተንፈስ ለማለት ቢሰባሰብ የድርጅቱን ቅድመ ጠንካራነት አመላካች ነውና የምንጠብቀው ነው። ግና ኢሕአፓ ከቶም እንዳያንሰራራ ፈላጊ ኃይሎች ቀላል አይደሉም። ይህ ሊከሰት የሚችል ሂደት የሚያመላክተን ኢሕአፓ ውስጣቸው ያለ፣ በድርጅቱ አመራሮች በማዘን ዳር ሁነው የሚያዩ፣ ያም ቢሆን ድርጅቱ ሲነካ፣ ከሌሎች አልፎ እርስ በርስ ታሪክና ድርጊት እየተዛባ ሲፃፍ ሲነገር ያማልና ነው ብዕሬን ከወረቀት ያገናኘሁት።

<u>ውድ አንባቢያን የኢሕአፓ ቤተሰቦች፦</u> ኢሕአፓ ምንም ችግር ቢኖርበት ውስጥ ሆኖ ማስተካከል ነው የሚገባው ብዬ ሰሜን አሜሪካን እንደመጣሁ በአንድ ዓመቴ ኢሕአፓን ተቀላቅዬ ከመከፈሉ በፊት ሁለት ዓመት ከተከፈለ በኋላ ሁለት ዓመት በአቶ መርሻ ኢሕአፓ ተካፍዬና ታግዬ ልበለው ነገሩ ሁሉ እጅግ አሳዛኝ ሆኖብኝ "እንኳን በቃኝ" ብዬ እራሴን ያገለልሁ ነኝ። ከአቶ እያሱና ከአቶ መርሻ ኢሕአፓ ወጣሁ እንጂ ኢሕአፓ ማኅተቤ ነው። ለዚህም ነው ከሁለቱ ኢሕአፓዎች በተለየሁ ማግስት "ያ ትውልድ ተቋም" ከ 8 ዓመት በፊት መሥርተን ሰማዕታት ወገኖቻችንን በመዘከርና የወቅቱን መረጃዎች በማሰባሰብ ክንዋኔ ላይ እየሠራን ያለነው። ለዚህ ደግሞ ድረ ገፃችንን (http://www.yatewlid.com, http://www.yatewlid.org ) መጎብኘቱ የሠራነውንና እየሠራን ያለውን መስካሪ ነው። ማነው እሱ? ለምትሉ በተለይ የሀገር ቤት ወገኖች በተጨማሪ የዛሬ 5 ዓመት "ፍፁም ነው እምነቴ፤ የከፍተኛ 15 ቀይ ሽብር እውነተኛ ታሪክ" ደራሲ ነኝ።

ወደ ተነሳሁበት ነጥብ ልምጣና የአቶ መርሻ ኢሕአፓ ወደ ሀገር በመግባቱ የድርጅቱን ስም ቢያስጠራም ግና ብዙ ጭቅጭቅ ሊያስነሳ እንደሚችል እገምታለሁ። በቅድሚያ ኢሕአፓ የራሱን ውስጣዊ ችግር ሳያጠራ እንደውም ኢሕአፓ ዴ ወይም ኢሕአፓ አ ተለጣፊ ስሙን ወዲያው ቀይሮና ኢሕአፓ ብሎ በአቶ መርሻ ሊቀ መንበርነት ሲገባ የአቶ እያሱ ዓለማየሁ ኢሕአፓስ? ተብሏል። በሁለቱም መሪዎች በኩል ኢሕአፓ ከተከፈለ በኋላስ ላለማጋነን አመራሮቹንና በጣት የሚቆጠሩ አባላቱ ሲቀሩ የተበተኑት አባላት ጉዳይስ? ይህ ሁሉ ሊያመጣ የሚችለው ችግር ግና ሊታይ አልተፈለገም። <u>*የኢሕአፓ ሁለቱ አመራሮችና የበተኗቸው የኢሕአፓ ወገኖች በአንድ መድረክ መጥተው በቅድሚያ በትንሹ ለ12 ዓመት እጅግ የተካረረ ፀባቸውን ለሀገርና ለሕዝብ እንዲሁም በሀገር ቤት ላሉት የኢሕአፓ ወገኖች ሲባል ጥረት ተደርጎና ይቅር ተባብለው በአንድነት መግባት ሲኖርባቸው*</u>

***አለመደረጉ ገና በድርጅቱ ላይ አላስፈላጊ አተካራ በቀጣይነት እንደሚያመጣና በመቶ ሺህ የሚቆጠር ወገኖችን በሀገር ቤት እንደሚያሳዝንና አንገት እንደሚያስደፋ መናገር ይቻላል።***

በአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ በኩል ያሉት የኢሕአፓ ወገኖች ጥሪው በተደረገ ማግስት እንደተከፋፈሉ ወደ ሀገር ለመግባት ቢወስኑ ከጠቀሜታው ይልቅ ጉዳቱ የጎላ ነበር። ያለ መግባታቸው ጠቀሜታው ግን በአቶ መርሻ ኢሕአፓ ጋር ስምምነት ላይ ሳይደረስ በመሆኑ እንኳንስ አልገቡ ያሰኛል። በዚህ ዕድሚያቸው እኔ ነኝ ኢሕአፓ እኔ የሚለውን አሳዛኝ ንትርክ ሀገር ቤት ገብተው እንኳን አልደገሙት። የአቶ ኢያሱ ኢሕአፓ አለመግባት በእርግጥ ለአቶ መርሻ ጠቅሟል። ኢሕአፓ እንዳልተከፈለ አድርገው ተጠቅመውበታል። ከላይ እንደገለጽኩት ማንም ይሁን ማን በውስጡ ኢሕአፓን አምቆ ያለው ወገናችን ሌላ ቢቀር መስዋዕት የከፈሉ ልጆቹን ለማሰብና ትዝታቸውን በዓይነ ኅሊናቸው ለመቅረጽ ይፈልጋሉና ቀና ምላሽ ቢሰጣቸው አያስደንቅም።

በዚህ የኢሕአፓ ሀገር ቤት መግባትና እንደገና መሰባሰብ ከበርካታ የኢሕአፓ ወገኖች ጋር ተወያይተናል። እጅግ በርካታ ወገኖች "ዝም ብላችሁ ተቀላቀሉ እንዴት ይባላል?" "በድርጅታችን በኩል የተሠሩ፣ ውስጣችንን የጎዱ፣ እስከዛሬ አፍነን የያዝናቸው ጉዳዮች ለመድረክ በቀተው በሚገባ ሳንወያይባቸው እንዴት ይሆናል?" ባዮች እንዳሉ ሁሉ "እራሳቸው አንድ ሳይሆኑ ግራ ሊያጋቡን አንፈልግምና በሩቁ!" ያሉም በርካታዎች ናቸው። በዚህ ጉዳይ የኢሕአፓ አባላት እንደገና ይሰባሰቡ ዘንድ ሙሉ በሙሉ በውጭ ያለውን ኢሕአፓን ሳያካትት ሀገር ቤት ያላችሁ ከጅምሩ ቀጥሉ፤ ከአንዱ ወግኖ የሚካሄድ ኢሕአፓ ለዳግም ጥፋት ይዳርጋልም፣ ሊሳካም እንደማይችል ስጠቁም ለአለፉት 12 ዓመታት በውጭ ያለነው የኢሕአፓ አባላትና የቀድሞ አባላት ምን ያህል እንደተናከስን በጽሁፍ (ለአብነት ያህል በየድረ ገጹ፣ በተለያዩ ሚዲያዎች ቃለ ምልልስ፣ በፓል ቶክ) በድምጽ፣ ያሉ መረጃዎች በርካታ መሆናቸውን ስለማውቅ ነው።

በሌላ በኩል ኢሕአፓን ለወጣቱ ለአዲስ አመራር እናስረክባለን ያሉት አቶ መርሻ እሰየው ቢያሰኝም በድርጅቱ ውስጥ የተከሰቱ ችግሮችን በግልጽ በማውጣት በተለይ ኢሕአፓ መከፈሉን፣ ሂደቱን በግልጽ በመግለጽ መሆን ነበረበት። ግና አንዱ አንዱን በመናቅ አቶ መርሻም በአቶ እያሱ ዓለማየሁ ሀገር አለመግባት ያገኙትን አጋጣሚ ሊጠቀሙበት ቢችሉም በአቶ እያሱ በኩል ሀገር ቤት የሚኖር የኢሕአፓ አባላት ብቻ ሳይሆኑ ኢሕአፓን በጥሞና የሚከታተሉ ወገኖች እንደሚኖሩ መገመት በተገባ ነበር። ከዚህ በመለስ ደግሞ የበላይነትን ለማግኘት ሲባል ሲዋሽ፣ የቅርብ ታሪክ ሲዛባ ብዙ ወገኖችን እንደሚነካ መገመት አግባብነት በኖረው። ለዚህም ነው የቅርቡን የወ/ሮ ቆንጂት ብርሐን ለኢሕአፓ መከፈል የሰጡት ምላሽ እጅግ አሳዛኝ ታሪክን የማዛባት ጉዳይ መታለፍ የለበትምና በመጠኑም ቢሆን የኢሕአፓን መከፈል ምክንያት አቀርባለሁ።

ወ/ሮ ቆንጂት ብርሃን በእርግጠኝነት በክፍፍሉ ወቅት ድርጅቱ ውስጥ አልነበሩም፣ ስላልነበሩ ስለመከፈሉ መናገር አይደለም መጽሐፍ ሊጽፉ ይችላሉ፤ ተፈላጊውን መረጃ ካገኙ። በኢሕአፓ በኩል የት ነበራችሁና፣ ምን ታውቃላችሁና ስለ ኢሕአፓ ታሪክ የምትጽፉ ሲባል ይሰማል፣ ይነበባል፡ ፡ ለዚህ ደጋግሜ የምለው አጭር መልሴ ለአብነት ያህል ነብሱን ይማርና ጳውሎስ ኞኞ የምንሊክን፣ የአፄ ቴዎድሮስን፣ ሌላም ታሪክና ገድላቸውን ሲያስነብብ አብሯቸው ዘምቶ፣ አብሯቸው ሁኖ እኮ አይደለም። ቀደም ሲል የተጻፉ መጽሀፍትንና የመሳሰሉትን በመመርከዝ፣ ታሪክ አዋቂዎችን በማናገር በጥቅሉ ተፈላጊ መረጃዎችን በማሰባሰብ ለመጽሐፍ አብቅቶ አስነብቦናል። እና 50 ዓመት በስደት የኖረ የኢሕአፓ አመራር ስለ ከተማው ትግል፣ ስለ ቀይ ሽብር፣ ስለ አደፍርስ አትናገርም፣ አትጽፍም ወዘተ ከተባለ ችግር ሊፈጠር ነው። ወ/ሮ ቆንጂትም በተለይ የኢሕአፓ ሊቀ መንበር ሁነው

ለሚናገሩት፣ ለሚጽፉት በእርግጠኝነት ትክክል መሆናቸውን ማወቅ ይጠበቅባቸዋል። በተለይ በኢሕአፓ ቀደምት ታሪክ ላይ። ለእኛ ኢሕአፓዎች ኢሕአፓ ዓላማ ነው። ያ ዓላማው ሲዛባ፣ ሲንሻፈፍ፣ ይሰማናል። ከአመራሩ ደካማነት የተነሳ ድርጅቱን ብንርቅም ይዞ የተነሳውን ዓላማ የሀገር ነውና በተለያየ መልኩ የምናንጸባርቅ በርካታዎች ነን።

በመሆኑም ወ/ሮ ቆንጂት "ኢሕአፓ የተከፈለው ወደ ሀገር ቤት እንግባ/አንግባ በሚል ምክንያት ነው" ሲሉ ሦስት ጉዳዮች ይንጸባረቃሉ፦

1) በጥቅሉ በዋህነት፣ በተባራሪ የሰሙትን አስታከው ያሉት ሊሆን ይችላል።
2) ይህንን ብንል እነ አቶ ኢያሱም ይህን ስለሚሉ አድማጭ ይቀበለናል የሚል ከበስተ ጀርባ ሌላ የአማካሪነት ያለበት ጉዳይ ነው ቢባል አያስኬድምን?
3) ሀገር ቤት ግልጽ ያልሆነ መረጃ ለሌለው ወገናችን መከፋፈሉ የመጣው ዶር ዐቢይ ጥሪ ከአደረጉ በኋላ እንግባ/አንግባ ተብሎ እንደተከፋፈለስ አያስመስልምን?

እስቲ ጥያቄ ላቅርብልዎ ወ/ሮ ቆንጂት

- ኢሕአፓ ከመከፈሉ በፊት በአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ በኩል 3 ገጽ፣ በአቶ መርሻ በኩል ባለ31 ገጹን ሠነድ አንብበው ነው ይህን ያሉት?
- ስለ አፊዳቪት ጉዳይ ሁለገብ የምንለውን የትግል ስልት አቁመን ወደ ሀገር መለስ ዜናዊን ይቅርታ ጠይቀን እንግባ/አንግባ የሚለው ውዝግብ በሦስተኛው የፓርቲው ጉባኤ በተደረገ ድምጽ አንግባ የሚለው ወገን አብላጫ ድምጽ አግኝቶ መዘጋቱን ያውቃሉን?
- ይህ ጉዳይ በዚህ ከተቋጨ በኋላ በኢሕአፓ ውስጥ የተከሰተው ውዝግብ በቅድሚያ በአመራር አካሉ ብቻ እንደነበር ጠንቅቀው ያውቃሉን?
- የኢሳት ጋዜጠኛ አልጠየቀትም እንጂ በአስቸኳይ ጉባኤ እንግባ/አንግባ በሚል የዛሬ 12 ዓመት ኢሕአፓ ከተከፈለ እንግባ ብሎ የወጣው የኢሕአፓ አካል በወቅቱ ለምን ወደ ሀገር ቤት እንደተባለው ይቅርታ ጠይቆ አልገባም? ላይገቡ ነው ወይ ድርጅት የከፈሉት? ቢባሉ ምን ይላሉ?
- አዎ አቶ እያሱ እንደሚሉት "የአቶ መርሻ ወገን ታዲያ ለምን ሀገር ቤት ሲገባ አይታይም" ሲባሉ "አይ ወያኔ እምቢ አላቸው" እርሶም ሊደግሙልን ይሆን?
- ክፍፍሉ ወደ ሀገር እንግባ/አንግባ በሚል እንዳልሆነ በሦስተኛው ጉባኤ አንግባ ካሉ አመራርና አባላት ውስጥ ወደ አቶ መርሻ ወገን ሲኖሩ እንግባ ያሉ ደግሞ ወደ አቶ እያሱ ወገን እንደነበሩ ያውቃሉን?

እነኚህን ነጥቦች ሳነሳ በኢሳት ውይይቶ ያስተላለፉት መልዕክት የፖለቲካ ጠቀሜታ ለማግኘት ከሆነ እጅጉን የተሳሳተ መሆኑን ለአንባቢ ላሳውቅ እወዳለሁ።

***<u>ኢሕአፓ ለምን ተከፈለ ለሚለው በቅድሚያ ሁለቱ አመራሮች ሹክቻና ዝና ፍለጋ አመራር አካሉን በቡድን ከፍለውታል።</u>*** ከዚያ ይህን የተካረረ ባህሪያቸውን ለመፍታት በአመራር ደረጃ ስላልቻሉ ለአባላት "መሥራት ስላልቻልን ጉባኤ ይጠራልን" ሲሉ አወረዱ። ከአጠቃላይ የድርጅቱ ጉባኤ በፊት የሰሜን አሜሪካ አህጉራዊ ጉባኤ ይጠራ/አይጠራ የሚል ውዝግብ ተነሳ። በዚህ ሂደት ሁለቱ አመራሮች የራሳቸውን ኃይል ለማሰባሰብ ዘመቻ ጀመሩ። በተለይ አቶ መርሻ በሥራ ጉዳይ ወደ ሰሜን አሜሪካ በመምጣት "ኢሕአፓ ሊፈርስ ነው" እያሉ ኃይል ያሰባስቡ እንደነበር በርካታ ታዛቢዎች አለንኮ። አቶ ኢያሱም አይዘዋወሩ እንጂ በስልክና በዲሲ ኢሕአፓ አባላት አማካይነት

ዘመቻቸውን ተያይዘውት እንደነበር ነው ታሪኩ። የዚህ ሂደት አባላቱን እጅግ በሚዘገንን ሁኔታ በሁለት ጎራ ያናከሱት የወቅቱ አመራር አባላት አልነበሩምን? የሰሜን አሜሪካው ጉባኤ ከብዙ ጭቅጭቅ በኋላ እንዲካሄድ ተወስኖ ለጉባኤው የመጡት አባላት አቀማመጥ፣ በእረፍት ሰዓት የሚደረግ ጭውውት ጎራ የለየና በመገለማመጥ አልነበረምን? በመጨረሻም ለቀጣዩ ዋና ጉባኤ የሰሜን አሜሪካው ወሳኝ በመሆኑ ለሰሜን አሜሪካ አህጉራዊ ኮሚቴ ለሚደረግ ምርጫ ማ ማንን መጠቆምና መምረጥ እንዳለበት አብዛኛው አባል ተነግሮትና ተዘጋጅቶ አልነበረም የተመጣው? ለዚህም በተለይ በሁለቱም ወገን እጩ ተመራጮች ለተለያዩ አባላት በተደጋጋሚ የሚቆጠረው ድምጽ 36 እንደነበር ምን ያህል የቡድን ሥራ እንደነበር በአካል የተመለከትን እጅግ በርካታዎች ነን። በጥቅሉ ከሰሜን አሜሪካው አህጉራዊ ጉባኤ አካሄድ ድርጅቱ እንዳበቃለት ወይም እንደሚከፈል ያለጥርጥር ጠቋሚ ነበር። አሁን ስለሀሳብ ልዩነት፣ ስለመወያየት ሳይሆን የቡድን ፉክቻው ቀጠለ። በየስቴቱ ያሉ የኢሕአፓ ኮሚቴዎች መነታረክ ያዙ፣ አመራሩ በሁለቱ ሰዎች አማካይነት ለዋናው ጉባኤ ይረዳ ዘንድ ዘመቻቸው ችግሩን ለመፍታት ሳይሆን አባላት ቁጥር ለማሰባሰብ ተሆነ።

ይህ በእንዲህ እያለ የኢሕአፓ ጽ/ቤት በአለበት በዲሲ በርካታ አባላት በመኖራችን በነበረው ሽሚያ ዲሲ ለሁለት ተከፍሎ ወደ ጉባኤው እንደተመጣ የሚታወቅ ነው። በዲሲ እንደታየው በመደበኛ ስብሰባ ታይተው የማይታወቁ ሁሉ አባል ነን እያሉ ለአንደኛው ወገን ሊወግኑ መምጣታቸው የሚዘነጋ አይደለም። በአስቸኳይ ጉባኤውም በውክልና ንትርክ ምክንያት ጉባኤው ለሁለት ቀናት እንዳልተጀመረ ነበር። በጉባኤው መጨረሻ ለሚደረገው አዲስ አመራር ምርጫ በአቶ እያሱ በኩል ለአመራር ምርጫ አብላጫ ድምጽ ማግኘታቸውን እስኪያረጋግጡ ጉባኤው እንዳይጀመር የተደረገው ጥረት አሜሪካ ተሆነ እንጂ ብዙ ጉድ በታየ። በአቶ መርሻም በኩል ጉባኤውን ረግጦ እንደሚወጣና በተወጣበት ወቅት ቀጥታ ወደ ተዘጋጀው ሌላ ምስጢራዊ ሆቴል አዳራሽ ተኪዶና የሁለት ቀን ስብሰባ ተደርጎ ኢሕአፓ ዴሞክራሲያ ተብሎ ወዲያውኑ ጋዜጣዊ መግለጫ በጽሁፍና በኢሳት መሰጠቱ በመረጃነት በብዙዎች እጅ ያለ ነው።

እውነት ወ/ሮ ቆንጂት ይህንን ሁሉ ዝርዝር ተጋርተዋል? የኢሕአፓ መከፈል እኮ የሁለት ጎረቤታሞች ፀብ አይደለም። በደምና በአጥንት የተሳሰረ ድርጅት፣ በወቅቱ ወደ 40 ዓመት ድርጅቱን በመሩትና በተለይ የሁለቱ አመራሮች ሹክቻና አምባገነናዊ ባህሪ ነው። ***<u>ይህ የ40 ዓመት ተመክሮ ያካበተ ድርጅት በራሳቸው በአመራሩ በኩል የተፈጠረውን ችግር፣ አለመግባባት በቅራኔ አፈታት ዘዴ መፍታት ተስኗቸው ጉዳዩን ወደ አባላት አውርደውና የራሳቸውን ቡድን ለመመስረት አባላቱን እርስ በርስ አናክሰውና ጎራ አስለይተው ኢሕአፓ የተከፈለበት ዋናው ምክንያት የድርጅቱ አመራር ሠርቶ የማያሠራና ውስጣዊ ዴሞክራሲ የሌለውና አምባገነናዊ ባህሪ በመላበሱ ነው።</u>*** ዛሬ አቶ መርሻ ሀገር ቤት ስለገቡ ይህ ታሪክ ከማህደር ሊሰረዝ አይችልም።

ለዚህ ደግሞ ከባለ 31 ገጹ የአቶ መርሻ ሠነድ ኢሕአፓ የተከፈለበትን አስቸኳይ ጉባኤ መጠራትን አስመልክቶ ይህንን ላስቀምጥ " . . . የተጠቆሙትን ችግሮችና ድክመቶች በቀና መንፈስ ተቀብሎ በጋራ መፍትሄ እንደመሻት ጥያቄዎቹን ለመጠየቅ "ማን የሞራል ብቃት አለው?" ተባለ። ለጥቆም "አንዳንድ የከአኮ (ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ) አባላት ድርጅቱን ሊበትኑ ተነስተዋል፣ ወደ ወያኔ ሊገቡ ተዘጋጅተዋል" የሚሉ መስመር የለቀቁ ሃሜቶች ተበራከቱ። አሉባልታና ስም ማጥፋት ዋናው ውስጣዊ የትግል ዘዴ ሆነ። መተማመንና መከባበር ጠፉ። አስቸኳይ ጉባኤ መጥራት ግድ ሆነ።" የጥቅሱ መጨረሻ። ጉባኤ ተጠራ ፓርቲው ተከፈለ። ለምን? በእልህና በፈጠራ ክሶች ብሎም በቡድን ሹክቻ።

በሌላ በኩልም በአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ የቀረበው ባለ 3 ገጽ ሠነድ ዋናውን ነጥብ ልጥቀስ:- "የአራተኛው ጉባዔ በሰየመው ከአኮ (ከፍተኛ አመራር ኮሚቴ) ውስጥ የሀሳብ አንድነት፣ መግባባትና ስምምነት በመጥፋቱ ምክንያት ድርጅታዊ ሥራዎችን በተገቢው መንገድ ለማከናወንም ሆነ ለትግሉ ተገቢና አመርቂ አመራር ለመስጠት አልተቻለም። በሀሳብና በአቋም ልዩነት የተወጣጠረው ይህ አካል ግዴታዎችን ለመወጣትም እራሱንም እንደ አካል እስከሚቀጥለው መደበኛ ጉባዔ ለማቆየት አስቸጋሪ ሆኖ ስላገኘው ይህን አስቸኳይ የድርጅት ጉባዔ መጥራት ተገድዷል።" በማለት ከአቶ መርሻ ቡድን ጋር ያለውን ባለ አራት ነጥብ ልዩነቶችን ሲያስቀምጥ "አፊዳቪት ፈርመን ሕጋዊ ሆነን እንቀሳቀስ፣ ሁለገብ ትግልን ትተን በሰላማዊ መንገድ እንቀሳቀስ፣. . . የሚሉ በአራተኛው ጉባኤ ይህንን አቋም የሚያንጸባርቁ አመራር ውስጥ በመግባታቸው ለመሥመር ልዩነት ተዳርገናል" ይላል።

እዚህ ላይ ሊታይ የሚገባው በአቶ ኢያሱ ሠነድ ድርጅቱ ምንም የፕሮግራምም ሆነ የዓላማ ልዩነት እንደሌለው እየታወቀ በሁለቱ ቡድኖች መሀል የመሥመር ልዩነት እንዳለ አቅርቦታል። በሌላ በኩል በሠነድ ያልቀረበ ግና በሰኔ 6 ቀን 2011 ዓ.ም. (June 13, 2009) VOA በተደረገ ቃለ ምልልስ አቶ መርሻ ጉዳዩን አቶ እያሱ ዓለማየሁ አመራሩ ሳያውቅ ኤርትራ በመጓዝ ከአቶ ኢሳያስ ጋር ተደጋጋሚ ግንኙነት ማድረጋቸውን ይጠቅሳሉ። ይህ ጉዳይ አንዱ አመራር በሌላው ላይ የበላይነት ለማግኘት የሚደርጓቸው እሰጣ ገባዎች ነበሩ። "የመሥመር ልዩነት፣ ሀገር ቤት ሊገቡ፣ ለወያኔ ድርጅቱን ሊሰጡ፣ አንጃዎች፣ ኤርትራ ጋር ግንኙነት ማድረግ፣ ወዘተ" ስም ልጠፋዎች በሁለቱም በኩል የነበሩት አመራሮች ችግሩን በቀና መንፈስ ከመፍታት ይልቅ በማጋጋል ድርጅቱ ይከፈል ዘንድ ያደረጉት አስተዋጽዖ ነበሩ።

ሌላው ግልጽ ሊሆን የሚገባው እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ሁለት ሠነዶች በአስቸኳይ ጉባኤው ቢቀርቡም በቂና አግባብ ያለው ውይይት አልተካሄደባቸውም። የጉባኤው የመጀመሪያ ሁለት ቀናት በውክልና ሳቢያ ሲጓተት ቆይቶ ጉባኤው ተከፍቶ አመርቂ ውይይት ሳይካሄድ ቅድመ ዝግጅት አድርጎ የመጣው የአቶ መርሻ ኢሕአፓ ወገን በሦስተኛው ቀን ጉባኤውን ረግጦ በመውጣት በዕለቱ የራሱን ሌላ ጉባኤ በማካሄድ ኢሕአፓ ዴ በማለት እራሱን ለሕዝብ አሳውቋል። ከዚያ በቀጣይነት በተለይ በአቶ ኢያሱ በኩል የሚሰጠው ቅጥያና ስም ማጥፋት ቀጠለ። ይበልጥ ሀገር ቤት ገብተን ከወያኔ ጋር እንሥራ ብለው ነው የሚለው ተደጋጋሚ ልፈፋ ቀጠለ። ወ/ሮ ቆንጂትም ይህንን ተገን አድርገው ይመስለኛል ለተጠየቁት ጥያቄ አጠናካሪ ምላሽ የሰጡት።

*__ከዚያስ ምን ተከነ__*

ሌላው መነሳት ያለበት ጉዳይ ኢሕአፓ ከተከፈለ በኋላ በሁለቱ አመራሮች የተካሄደው ብተና ነው። ድርጅቱ ሲከፈል የተከፈለው አባላት ቁጥር በሁለቱም በኩል ተመጣጣኝ ቁጥር ነበር። ከተከፈለ በኋላ በንዴትና በቁጭት ከሁለቱም ሳይወግኑ የግል ውሳኔአቸውን በመውሰድ ከድርጅቱ እራሳቸውን ያገለሉም ነበሩ። ድርጅቱ የተከፈለበት ዋናው ምክንያት በአመራር ችግር በመሆኑ እንደተከፈለ በአቶ መርሻ በኩል ያለነው በአደረግነው ጉባኤ መልሶ አቶ መርሻና ከመከፈሉ በፊት አመራር የነበሩ ደግመው የአመራርነቱን ቦታ በመያዛቸው "ድርጅቱ የተከፈለው ከአንድ አምባገነን ወደ ሌላ ለመገላበጥ አይደለም" በማለት እራሱን ከአቶ መርሻ ቡድን ያገለለ አንድ ሰው ብቻ ነበር። ይህንን አባባሉን በእርግጠኝነት ኢሕአፓ በተከፈለ በዓመቱ በአቶ መርሻ አመራር ቡድን ዳግም አባላቱን አላሠራ ማለቱና መከፋፈልና ማባላት እየጎላ በመምጣቱ በአቶ መርሻ በኩል የነበርነው ባለማጋነን ሁለት ሶስተኛው አባል ሙሉ በሙሉ ድርጅቱን ሊለቅ ችሏል። ይህ የአቶ መርሻና የቡድኑ ሂደት ኢሕአፓን ከመክፈል አልፎ ድርጅቱን በትኖታል። ታሪኩ ይህ ነው። በትንሹ ወደ ሦስት አመራር

አባላትና ወደ ሰባት አባላት በአሳፋሪ መልክ በደብዳቤ የአቶ መርሻ ቡድን ከድርጅቱ ማባረሩ በመረጃ ያለ ጉዳይ ነው። ኢ.ሕ.አ.ፓ ዴ በተከፈለ ዓመት ተኩል የአቶ መርሻው ኢ.ሕ.አ.ፓ ዴ ተበትኖ በጥቂት አመራር አካላትና በጣት በሚቆጠሩ አባላት እንደ እድር ስብስብነት ለአለፉት 10 ዓመታት የተጓዘ ቡድን ነው።

በተመሳሳይ መልኩ በአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ የሚመራው ኢ.ሕ.አ.ፓ በውስጥ በነበረው ሹኩቻ በርካታ አባላቱን በትኗል። በተለይ ወክንድ (ወጣት ክንፍ) በሚል ወጣቶችን በማሰባሰብ ጥሩ ጥረት ያደረጉትንና እውነትም ጠንከር ያሉ ወጣቶች በመሰባሰብ ኢ.ሕ.አ.ፓን በውጭው እያንቀሳቀሱ የነበሩትን በሙሉ በማባረር አሳፋሪ ተግባር ተፈጽሟል። የዚህም ሂደት ውጤት በአቶ ኢያሱ የሚመራው ኢ.ሕ.አ.ፓም ከአመራር አባላቱና በጣት ከሚቆጠሩ አባላቱ ጋር ዛሬም ይጓዛል። ይህ ነው እንግዲህ የውጭው ኢ.ሕ.አ.ፓ ሕይወት።

ኢ.ሕ.አ.ፓ ተበትኖ እኔም የአቶ መርሻን ኢ.ሕ.አ.ፓ ለቅቄ ከወጣሁ በሁዋላ "ኢ.ሕ.አ.ፓን እናድን" ግንቦት 24 ቀን 2002 ዓ.ም. (June 01, 2010) በሚል ጽሁፌ ገጽ 4 ይህን አስነብቤ ነበር፦

". . .ኢ.ሕ.አ.ፓ ተከፍሎ ኢ.ሕ.አ.ፓዴ እራሱን ይፋ ባደረገ ሁለት ዓመት ሳይሞላው የተከሰተው ችግር ከበፊቱ በምንም አይለይ። አሁንም የተነሳው ጥያቄ ሥር ቶ ማሰራት ያቃተው አመራር ላይ ያነጣጠረ፤ ፓርቲውን የማጠናከርና የማንቀሳቀስ ጉዳይ ነበር። ዳግም ይህ ጥያቄ በፓርቲው (በኢ.ሕ.አ.ፓ ዴ) ሊከሰት የቻለውም ፓርቲው ተከፈለ እንጂ ኢ.ሕ.አ.ፓ ዴ ፓርቲው የተከፈለበትን መሠረታዊ የድርጅቱን ችግሮች ሊመለከት የተዘጋጀም አልነበረም። በረዥም ጊዜ አመራር ዘመናቸው ባሰፈኑት ቡድናዊ ስሜት ፓርቲውን የሁለት አመራሮች (አቶ መርሻና አቶ ኢያሱ) የገመድ ጉትቻ እስከነችግሩ ከፈለው እንጂ ሁለቱም ለውጥ አጋች ናቸው። አሁንም የፓርቲውን መሠረታዊ ችግር ለመዳሰስ ከመጣር ይልቅ እየታመስን ያለነው በአሉባልታና በፈጠራ ክሶች ነው። በፈጠራ ውንጀላ አባላት ታግደዋል፣ ተባረዋል። ጥያቄና ሀሳብ አቅራቢዎች ወደ ዳር ተገፍተዋል፣ ሌሎችም ሁኔታውን እያዩ ዝምታን መርጠዋል።

"ኢ.ሕ.አ.ፓ በመከፈሉ የትኛውም ወገን አሸናፊ እንደማይሆን እየታየ አሁን ያለበት ሂደት ላይ ደርሰናል። የሀሳብ ልዩነትን በኃይል፣ በትዕቢት፣ በዱላ የማስተናገድ ውጤት ፓርቲውን ከፍሎ ቀጣይ መባላትንና መበታተንን በሁለቱም አቅጣጫ እያሳየ ነው። <u>መሠረታዊ የፓርቲውን ችግሮች ገምግሞና ተወያይቶ የተደረገ መከፋፈል አልነበረምና፤ የጥቂት አመራሮች ግላዊ ሹክቻና የራሴ ሀሳብ ብቻ መሰማት አለበት አባዜ ፓርቲውን ከፍሎ ሁለቱም በተመሳሳይ ጎዳና ጉዟቸው መሰናከል እንጂ ዕድገት፣ ድክመት እንጂ ጥንካሬ አስመዝጋሚ አልሆነም።</u>

"ኢ.ሕ.አ.ፓ ያለበትን ከባድ ፈተና መፍታት ካቃተን ወዴት ልናመራ እንደምንችል በመገንዘብ ከዚህ አሳፋሪ ውድቀት ለመዳን ከተፈለገ "ምን መደረግ አለበት?" በሚለው ላይ ተወያይቶ አመርቂ መፍትሄ ፍለጋ መረባረብን ይጠይቃል። . . ." የጥቅሱ መጨረሻ።

ዛሬም ከ 12 ዓመት መከፋፈል በኋላ ያለነው እዚሁ ላይ ነው።

ሌላው አሳፋሪና የቅጥፈት አካሄድ የተከሰተው ከአቶ ኢያሱ ኢ.ሕ.አ.ፓ ከለቀቁት ውስጥ ጥቂቶችን ወደ አቶ መርሻ ኢ.ሕ.አ.ፓ በማስገባት በሰኔ 27 ቀን 2007 በወጣው ጋዜጣዊ መግለጫ ኢ.ሕ.አ.ፓ አንድ ሆነ በማለት በማወጅ ስሙን ከኢ.ሕ.አ.ፓ ዴ ወደ ኢ.ሕ.አ.ፓ አ (ኢ.ሕ.አ.ፓ አንድነት) ቀይረው ጋዜጣዊ መግለጫ በማውጣት፣ ኢንተርቪው በመስጠት፣ በሚደረጉ ስብሰባዎች አንድ ሆንን በማለት እጅግ

አሳፋሪ የሀሰት ፕሮፓጋንዳ መነዛቱን በውጭው ዓለም ያለው ፖለቲከኛ በሚገባ ያውቀዋል። በዚህ ወቅት ይህንን ቅጥፈት በማጋለጥ ሐምሌ 21 ቀን 2007 ዓ.ም. በጻፍኩት ጽሁፍ የአቶ መርሻ ቡድን እንደተበሳጩ እረዳለሁ። ግና በኢሕአፓ ስም ፖለቲካ ውሸት ሊሆን አይገባውም። አሁንም በወ/ሮ ቆንጂት የኢሕአፓ መከፈል ጉዳይ መረጃው ብቻ ወደ 10 መጽሐፍ ሊያጽፍ የሚችል ገና ለሕዝብ ይፋ ያልሆነ ጉዳይ እያለ እንደ ቀላል ጉዳይ ያውም የተሳሳተ ምክንያት የሚያየን፣ የሚሰማን፣ የሚያደምጠን የለም ተብሎ ከሆነ እኛም ኢሕአፓ ነንና ዝም አንልም። ገና ለወደፊት በኢሕአፓ ስም ለሚደረግ እንቅስቃሴ መሠረታዊ ዓላማውን የሳተ አካሄድ ተግባራዊ ከሆነ አሁንም ድርጅቱን ታሪክ እንደምንከታተለው፣ ጉዳዬ ከኢሕአፓ እንጂ ከአመራሮቹ ባለመሆኑ ከመጻፍ፣ ከመናገር የሚለየኝ እንደሌለ ልገልጽ እወዳለሁ። በዚህ አጋጣሚ በአቶ መርሻ በኩል የማውቃችሁ የአመራር አካላትና አባላት እውን ኢሕአፓ የተከፈለው ሀገር ቤት እንግባ/አንግባ በሚል ንትርክ ነውን? ምላሻችሁን ብትሰጡኝ ደስ ይለኛል።

ከላይ እንደገለጽኩት ከላይ ላሰፈርኳቸው እያንዳንዱ ድርጊቶች መረጃዎቹ በእጄ አሉ። መረጃ በእጄ ይገኘ ነው የጻፍኩት። አሁን ይህንን ልጽፍ የተነሳሁት የሀገር ቤቱ ኢሕአፓ መሪ ወ/ሮ ቆንጅት በኢሳት አዲስ አበባ "በየዋህነት" የሰጡት ታሪክን ያዛባ አባባል በአጭሩ ካልተነገረ ነገ ሌላ እንዳይቀጥል በማለት ነው። ይህ የመከፈል ጉዳይ ኢሕአፓ ያለፈበት አንድ የታሪክ ምዕራፍ ነውና ልንዋሸለትም፣ ልንደብቀውም አይገባምና ስለ ክፍፍሉ ወደፊት በሚወጡ መጽሐፍት ያሉ መረጃዎች የመጽሐፉ አካል ይሆናሉ። ሕዝብ፣ የኢሕአፓ ልጆችና አዲሱ ትውልድ ማወቅ አለባቸውና።

***<u>ምን መደረግ አለበት</u>***

ኢሕአፓ አሁን ከሁለት አልፎ ሦስት ነው። አንደኛው በአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ የሚመራው፣ ሁለተኛው በአቶ መርሻ አመራር አባልነት በወ/ሮ ቆንጂት ብርሃን የሚመራው፣ ሦስተኛው እጅግ አብዛኛውን አባላት የያዘው ከ1967 ዓ.ም. ጀምሮ በኢሕአፓ በአባልነት፣ በደጋፊነት ተሳትፎ ዛሬ በሕይወት ያሉት አንጋፋ የኢሕአፓ የቀድሞ አባላት፣ ደጋፊዎች፣ ቤተሰቦች ኢሕአፓ ሲጠራ የሚነዝራቸው፣ ውስጣቸው ሁሌም ያለ ግና ድርጅቱ እንዴት ሊሰባሰብ ይገባዋል ብለው በቁጭት የሚመለከቱ ሲሆኑ፣ ሌሎች ደግሞ በተለይ በውጭው ዓለም በሁለቱ አመራሮች ዝና ፍሊጋ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ከኢሕአፓ በቁጭት የራቁ ጠንካራ የቀድሞ አባላቱ ናቸው።

ይህንን ሁሉ ኢሕአፓ "የቀደመ ዳቦ በላ" በሚል ጨዋታ በሽቅድምድም እኔ ነኝ ኢሕአፓ ሊባል አይገባውም። ኢሕአፓ በሀገር ቤት ስሙ መጠራቱን ብደግፈውም ሌሎቹን አራግፎ እኔ ነኝ ማለት ለጊዜው ያሰባስብ ይሆናል እንጂ ኢሕአፓን በጠንካራ መልኩ አያነሳውም። ምክንያቱም መላውን አባላትቱን አካቶ የተካሄደ ሂደት አይደለምና። ኢሕአፓ ለአለፉት በርካታ ዓመታት በደርግ ዘመን ከግድያው ባሻገር እንደ ሀገር አስገንጣይና አጥፊ ሲዘመትበት፣ በወያኔም ዘመን ሀገር ሊበትን፣ ሊያጠፋ፣ ገዳይ ተደርጎ ለአሁኑ ትውልድ ሲሰበክ፣ የደርግ አባላቱ እየወነጀሉ ሲጽፉበት ያለ ድርጅት ነው። በመሆኑም <u>ኢሕአፓ ለፖለቲካ ትግል ከመቸኮሉ በፊት ገጽታውን ማጽዳት ይገባዋል።</u> ለዚህ ደግሞ በቅድሚያ አሁንም በራሱ ውስጥ የይቅር መባባልን መድረክ ከፍቶ ወደ አንድ ካልመጣ በምንም መልኩ ከተመሳሳይ መነታረክ አያመልጥም። ስለሆነም

1. የመጀመሪያ እርምጃ

- በአቶ ኢያሱ ዓለማየሁ በኩል ያለው የኢሕአፓ አካል በቅድሚያ በተለያየ ምክንያት ያባረሩዋቸውንና የራቁትን አባላቱን ይቅርታ ጠይቀው ማስባሰብ ይኖርባቸዋል። ይህም ትልቅነት ነው።

- በአቶ መርሻ ዮሴፍ በኩል በቅድሚያ በተለያየ ምክንያት ያባረሩዋቸውንና የራቁትን አባላቱን ይቅርታ ጠይቀው ማሰባሰብ ይኖርባቸዋል። ይህ የትልቅነት ምልክት ነው።

2. ቀጣይ እርምጃ

- የመጀመሪያው እርምጃ ተግባራዊ በማድረግ በቀጣይነት በአቶ ኢያሱ ዓለማየሁና በአቶ መርሻ ዮሴፍ በኩል ያለው ኢሕአፓ እስካሁን የተሥሩ ስህተቶችን ይቅር በመባባል ለሀገርና ሕዝብ እንዲሁም ለድርጅቱ ስም ሲባል እንደጥንቱ ወደ አንድ ኢሕአፓ መምጣት ይኖርባቸዋል። ሁለቱም ቢያንስ ዕድሜ ሊገዛቸው ይገባል።

3. ሦስተኛ ደረጃ

- ወደ አንድ የመጣው ኢሕአፓ በመግባብት እየተጓዘና ሀገር ቤትም በውጭው ዓለምም እየተንቀሳቀሰ በተለይ በሀገር ቤት ያለውን የኢሕአፓ ኃይል በማሰባሰብ በድርጅቱ የተለያዩ ጉዳዮች ላይ ግልጽና ቀና ውይይት ለሕዝብ ክፍት የሆነ መደረግ ይኖርበታል። በዚህ ውይይት እጅግ በርካታ የቀድሞ የኢሕአፓ አባላት የሚያውቁትን፣ የተደረጉ፣ የተሰማቸውን ይገልጹ ዘንድ ሰፋ ያለውን ዕድል መስጠት

4. አራተኛ

- እነኚህ ጉዳዮች በቅደም ተከተል ከተጓዙ አንድ የሆነው ኢሕአፓ በአዲስ መልክ ያሰባሰባቸውን አካቶ ጉባኤ በማድረግ <u>*ኢሕአፓ በፖለቲካው ቀጥሎ ለመንግስት ሥልጣን መጓዝ ይሻለዋል ወይስ እንደ አንድ ኢንስቲትዩት ተቋም ሁኖ በአለው ተመክሮ የፖለቲካ ማስተማሪያና ልምድ መቅሰሚያ ይሁን?*</u> የሚለውን ተወያይቶ በአባላቱ ፍላጎት መሠረት መጓዝ። ኢሕአፓን አዲስ ትውልድ ይረከበው ከተባለ ስለ ምርጫ የሚታሰብበትና የሚቸኮልበት ጉዳይ የለምና ከላይ ያቀረብኳቸው ነጥቦች ተቀባይነት አግኝተው ወደ ተግባራዊነቱ ከተገባ ይህ የአንድነት ጉባኤ ኢሕአፓ እራሱን ለህዝብ ይፋ ባደረገበት ነሐሴ 26 ቀን 2012 ዓ.ም. ሊታሰብበት ይቻላል።

<u>*ጥርጣሬ*</u>

እነኚህ ከላይ የተጠቀሱት ሁኔታዎች ተግባራዊ ካልሆኑ በተለይ የሁለቱ ኢሕአፓዎች አንድነት ተግባራዊ ካልሆነ ኢሕአፓ በሀገር ውስጥ የተሳካ እንቅስቃሴ ይኖረዋል ማለት አስቸጋሪ ነው። በአቶ ኢያሱ የሚመራው ኢሕአፓ ሀገር ቤትም አባል እንዳላቸው መገንዘብ ይኖርብናል። በመሆኑም በውጭው ያለነውስ ለምደነዋል ሀገር ቤት ያሉትን ቆስቁሰን ለሌላ ፀፀት ባንዳርጋቸው መልካም በመሆኑ ከኢሕአዴግ/ብልጽግና የምርጫ ቧልት እርቀን ሌሎች እየሠሩ ካሉ ወገኖች በኢሕአፓ ስም ታሪኩን ማሰባሰቢያ፣ ሰማህታቶቹን መዘከሪያና ትውልድ ማስተማሪያ ኢንስቲትዩት ተቋም ላይ ትኩረት ቢሰጥ ሀሳቤን አቀርባለሁ። ለዚህ ደግሞ ለአለፉት 8 ዓመት እየተንቀሳቀሰ ያለውን ያ ትውልድ ተቋም፣ ቤዛ ኢትዮጵያ የከርቸሌ ልጆች ስብስብ፣ የቀይ ሽብር ሰማዕታትን ሌሎችም ካሉ አካቶ እጅግ ብዙ ተግባራትን ማከናውን ይበጃል ባይ ነኝ።

ሌላው አማራጭ በምንም መልኩ በአቶ ኢያሱም በአቶ መርሻም የሚመራውን ኢሕአፓ ሳያካትት ሙሉ በሙሉ የሀገር ቤት ኢሕአፓዎች ብቻ እራሳችሁን አደራጅታችሁ የሀገር ቤቱን ኢሕአፓ አጠናክራችሁ ቀጥሉ። በዚህ ጉዳይ በአመራር አባልነት፣ በአማካሪነትም ሆነ በማንኛውም ጉዳይ የአቶ ኢያሱና የአቶ መርሻ ኢሕአፓ አንድ ሆነው ካልመጡ እዛው የውጭው ኢሕአፓቸውን ይዘው ይቀጥሉ እላለሁ። እውነት እላችኋለሁ ሀገር ቤት ያላችሁ ኢሕአፓዎች ይህን ያደረጋችሁ ጊዜ ሌላ ቢቀር ያለ ጭቅጭቅ ትጓዛላችሁ።

**ማጠቃለያ**

ኢሕአፓ ታሪኩን ለመጠበቅና ከፖለቲካውም ባሻገር በርካታ ልናከናውናቸው የሚቻሉ ጉዳዮች መኖራቸው አሌ አይባልም። ከላይ ያቀረብኳቸው የይቅርታ መንገዶች ሁሉም ያጠፋውን ለመወቃቀስ ጥፋቶችን እያነሱ ለመነጋገር ሳይሆን በበጎ መንፈስ ተጀምሮ ምን እናድርግ? ወደ ሚለው ሕዝብንና ሀገርን የማገልገል ተግባር ላይ በአንድነት ከተነሳን ብዙ መሥራት ይቻላል።

ከዚህ በዘለለ ሁኔታዎች ከረው ሁሉም በየፊናው ከተጓዘ ግና በኢሕአፓ ስም የሚደረጉ መሠረታዊ ስህተቶች መታለፍ እንደማይኖርባቸው እኔም ኢሕአፓ ነኝ እላለሁኝ።

ኢሕአፓ የሕዝብ ሀብት ነው!!!

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

ፈጣሪ ኢትዮጵያን ይባርክ!

ቸር ይግጠመን!!!


ነሲቡ ስብሐት ከሰሜን አሜሪካ

(703) 300 4302

nhsibhat@gmail.com


ታህሳስ 29 ቀን 2012 ዓ.ም. (January 07, 2019)